# <u>በአዲስ ሕይወት ማደግ</u>

## <u>የቃል ጥናት ክፍሎች፡-</u>

**1ጴጥ፡2፡2፡-**ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።

**ቆላ፡3፡16፡-**የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።

**ዕብራ፡10፡24-25፡-**ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።

**ገላ፡6፡10፡-**እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።

**መዝ፡92፡1-2፡-**እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው ልዑል ሆይ ለስምህም ዝማሬ ማቅረብ በማለዳ ምሕረትን በሌሊትም እውነትህን ማውራት።

## <u>አራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች</u>

1. ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ?
2. ከእግዚአብሔር ጋር በጥሩ ግንኙነት እንድታድግ ይህ ታሪክ የሚያስተምርህ ምንድነው?
3. ዳግመኛ የተወለደ ክርስቲያን ማድረግ የሚፈልገው ነገር ምንድነው?
4. ይህንን ታሪክ በዚህ ሣምንት እንዴት ከሕይወትህ ጋር ታዛምዳለህ?
5. ይህ ታሪክ ትኩረት የሚያደርገው ምኑ ላይ ነው? በመንፈሳዊ እድገት አንተን ሊረዳህ የሚችል ምንድነው?

## <u>ታሪኮች</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ሉቃ፡2፡42-52 | በመፈንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ መትጋት |
| 2. | ሕዝ፡1፡28-3፡3 | ቃል፡ ሕዝቅኤል |
| 3. | ምሳ፡2፡1-5 | ቃል |
| 4. | ዕብ፡12፡1-11 | የአባት ተግሣጽ |
| 5. | ዳን፡6፡10-24 | ፀሎት |
| 6. | ማቴ፡6፡5-13 | ፀሎት |
| 7. | ሐዋ፡2፡42 | ሕብረት ማድረግ |
| 8. | ሐዋ፡4፡32-36 | መስጠት |
| 9. | ዮሐ፡13፡1-17 እና ቁ.34-35 | አዲስ ትዕዛዝ |
| 10. | ማቴ፡25፡31-46 | ወንድሞችን መውደድ |
| 11. | ሐዋ፡9፡32-43 | አገልግሎት |
| 12. | ዮሐ፡4፡27-38 | የአባትን ፈቃድ ማድረግ |
| 13. | 2ነገ፡2፡1-15 | የኤልሳ ከአለቃው (ከጌታው) ጋር መቆየት |
| 14. | 1ሳሙ፡18፡1-4 | ዮናታንና ዳዊት |
| 15. | 1ሳሙ፡20፡1-42 | እርስ በርስ መዋደድ |
| 16. | ሮሜ፡12፡1 | አምልኮ |
| 17. | መዝ፡100 | አምልኮ |

__ለመሪው፡-__

- የእነዚህ ታሪኮች ቅደም ተከተል አማኞች በጌታ እንዲያድጉ ያበረታታቸዋል፡፡ እንደመሪ የቡድንህ አባላት በጌታ እንዲያድጉ በሚረዱ ዋና ነጥቦች ላይ ትኩረት አድርግ፡፡ ታሪኮችን በጥሩ ሁኔታ ለመናገር የሚረዱ ደረጃዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ ታሪኮችን ማወቅ የቡድኑ አባላት ታሪኩን እንዲያሰላስሉትና ተጨማሪ ነገር እንዲማሩ ይረዳቸዋል፡፡
- <u>አሁን ጀምር</u>፡፡ የቡድንህ አባለት ባለፈው ሳምንት ምን እንደተማሩ አሁን ምን እንደሚማሩና ታሪኩን እንዴት ከሕይወታቸው ጋር እንደሚያዛምዱ ጠይቃቸው፡፡ ታሪኩን ለሌላ ሰው ለመናገር አጋጣሚ ያገኘ ሰው አለ?
- ታሪኩ በሚነገርበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ መዘጋት አለበት፡፡የታሪኩን ዋና ሀሳብ ተናገር እንጂ ‹አንድ በአንድ እናገራለሁ› ብለህ አትሽምድድ፡፡ ታሪኩን ሁለት ጊዜ ተናገር፡፡ ‹‹ ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ታሪክ ነው…›› በማለት ታሪኩን መናገር ጀምር፡፡ እንዲሁም ደግሞ ታሪኩን ስታጠናቅቅ ‹‹ ይህ የቃሉ ታሪክ ነው›› በማለት ታሪኩን ጨርስ፡፡
- አሁን የቡድኑ አባላት ታሪኩን እንዲናገሩ ዕድል ስጣቸው፡፡ አንድ ሰው ሲናገር ሌሎች መርዳት ይችላሉ፡፡ ይህ ታዲያ የቡድኑ አባላት በሙሉ የሚሳተፉበት ስለሆነ ድፍረትን ይፈጥርላቸዋል፡፡ ታሪኩን ለመረዳት የሚረዱ ጥያቄዎችን ማንሳት ትችላለህ፡፡ ለምሳሌ፡- በመጀመሪያ ምን ሆነ? በዚያ ሥፍራ ማን ነበር? እነርሱ ምን አደረጉ? ቀጥሎስ ምን አደረጉ? ሌላው ሰው ምን አደረገ? ወይም ምን አለ?
- አሁን ታሪኩን ከእግዚአብሔር ቃል አንብብ፡፡
- ከመሠረታዊ ጥያቄዎች አንዱን ጠይቅ፡- ‹የታሪኩ ዋና ሀሳብ ትርጉም ወይም ትኩረት ምኑ ላይ ነው› በዚህ ጥያቄ ላይ ውይይት አድርግ፡፡
- አሁን እያንዳንዱ ሰው ታሪኩን ይናገራል፡፡ ሌሎች የቡድኑ አባላት የሚናገረውን ሰው መርዳት ይችላሉ፡፡ አሁን ቡዱኑ ታሪኩን ለ7 እና 8 ጊዜ ሰምቷል፡፡ ይህንን ወደ ቤታቸው ሲሄዱም ለሌሎች ጎረቤቶቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው በመናገር እንዲለማመዱ አበረታታቸው፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት ይህንኑን ታሪክ ለሌላ ሰው እንዲመሰክሩ ንገራቸው፡፡ ይህን ሁሉ አድርገህ ስትጨርስ ጊዜ ካለህ የውይይት ጥያቄዎችን መጀመር ትችላለህ፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት ታሪኩን በቤታቸው ለማን እንደተናገሩና ታሪኩን በመናገራቸው የሆነውን ነገር ጠይቃቸው፡፡ የውይይት ጥያቄዎች ከመጀመራቸው በፊት ይህ ጥያቄ መጠየቅ አለበት፡፡
- የውይይት ጥያቄዎች ውይይቱ በሚገባ እንደካሄድ ይረዳሉ፡፡ ነገር ግን አራቱን መሠረታዊ ጥያቄዎች ወይም ሌሎችን ጥያቄዎች ፈጥረህ መጠየቅ ትችላለህ፡፡ ነገር ግን ከታሪኩ መውጣት የለብህም፡፡
- ታሪኩን በሚቀጥለው ሳምንት ተዘጋጅተው እንዲናገሩ ከቡድንህ አባላት የተለያዩ ሰዎችን ወክል፡፡

# ትምህርት-1

## በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ መትጋት

***መግቢያውን አንብብ***፦ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኛችን አድርገን ስንቀበል ዳግመኛ ተወልደናል ማለት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ቤት አዲስ እንደተወለዱ መንፈሳዊ ሕፃናት እንሆናለን፡፡ እግዚአብሔር አባታችን ይሆናል፤በሚያስፈልገን ሁሉ እየረዳን እንደ አባት ያሳድገናል፡፡ በአሜሪካን አገር የተደረገ አንድ የቤተክርስቲያን ጥናት ይፋ እንዳደረገው 85% የሚሆኑ አዲስ አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወት በሕፃንነት ደረጃ ይቆያሉ፡፡ ዛሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማደግ ያሳየውን ትጋት እንመለከታለን፡፡ ኢየሱስ 12 ዓመት ሲሆነው እርሱ በነበረበት ባሕል 12 ዓመት የሆነው ሰው ጎልማሳ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ ሰዎች የሚጎዳቸው ነገር እንዳይነካቸው በቡድን ይሄዱ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ሕፃናትና ሴቶች ከፊት ሲራመዱ ወንዶች ከኋላ ይከተሉ ነበር፡፡ ስለዚህ 12 ዓመት የሆነው ሰው ከፊት ወይም ከኋላ መሆን ይችላል፡፡ ታሪኩ ከሉቃስ ወንጌል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፦ ሉቃ፡2፡42-52

የት? ምን? መቼ? ለምን? ማን? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን ግልጽ አድርግ፡፡

ታሪኩን አንብብ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. በቤተ መቅደስ ውስጥ ለነበሩ አስተማሪዎች ኢየሱስ ያደረጋቸው ሁለት ነገሮች ምን ነበሩ?
2. ኢየሱስ ለእድገቱ እንዲረዳው ያደረገው ነገር ምን ነበር? ቁ.46, 49, 51, 52 ተመልከት፡፡
3. 1ጴጥ፡2፡2 አንብብ፦ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምን እንድናደርግ ነው? ይህንን ነገር ኢየሱስ እንዴት በታሪኩ ውስጥ አሳየ?
4. አንድ አማኝ ዳግመኛ ስለ ተወለደ በውስጡ የሚፈጠሩ መልካም ምኞቶች ምንድናቸው?
5. ከእግዚአብሔር ጋር ስላለህ ግንኙነት ዛሬ የተማርከው ምንድነው?
6. በግልህ መንፈሳዊ ሕይወትን እንዴት ትጠማለህ? ራስን መስጠት በመንፈሳዊ እድገትህ ላይ ምን ዓይነት ልዩነት ያመጣል?
7. ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ለማደግ እንዲረዳህ በዚህ ሳምንት ምን ማድረግ አለብህ?

**የቃል ጥናት ክፍል፦ 1ጴጥ፡2፡2፦**

ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ፡፡

## ትምህርት-2

**ቃል፡- ሕዝቅኤል**

**መግቢያውን አንብብ፡-** ሕፃናት ቶሎ ቶሎ መመገብ አለባቸው፡፡ አንድ ሕፃን በቂና ገንቢ ምግብ ካላገኘ ይታመማል፤ደካማም ይሆናል፡፡ ታሪኩን ከእግዚአብሔር ቃል ስንናገር ስለዚህ ጉዳይ አስብ፡፡ በተለያዩ ነገሥታት ዘመን የእሥራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ አምጸው ነበር፡፡ እነርሱ ክፉዎች ስለ ነበሩ እግዚአብሔር በነቢያት በኩል ስለ ክፋታቸው ንስሐ እንዲገቡ አስጠንቅቋቸው ነበር፡፡ በመጨረሻም በባቢሎናዊያን እጅ እንዲወድቁና ወደ ሩቅ አገር በባሪነት እንዲወሰዱ እግዚአብሔር ፈረደባቸው፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይወድ ስለነበረ በነብዩ ሕዝቄል በኩል ተናገራቸው፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ክብሩን በራእይ ለሕዝቄል ገለጠ፡፡ ቀጥሎ የሆነው ነገር ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡- ሕዝ፡1፡28-3፡3፡- ማን? ምን? የት? ቀጥሎ ምን ሆነ? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡

ታሪኩን አንብብ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ሕዝቄል የእግዚአብሔርን መልእክት ይዞ ወደ ሕዝቡ መሄዱን የፈራው ለምንድነው?
2. መጽሐፉ ምንን ያመለክታል?
3. መጽሐፉን መብላት የሚለው ምንን ያመለክታል?
4. ሕዝቄል በድፍረት ወደ ሕዝቡ እንዲሄድ የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ሊረዳው ይችላል?
5. ምግብ መብላት እኛን ምን ያደርገናል? መቼ መቼ ነው ምግብ መብላት ያለብን? ይህ ለውጫዊ አካል የምግብ አስፈላጊነት ለእግዚአብሔር ቃል ስለሚኖረው አስፈላጊነት ምን ያስተምረናል?
6. መዝ፡19፡7-10 አንብብ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለመግለጽ የተጠቀሙ ቃላቶች የትኞቹ ናቸው?
7. ስለ እግዚአብሔር ቃል ምን ትማራለህ?
8. ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረታችንን አጠናክረን በመንፈሳዊ ሕይወት እንድናድግ የሕዝቄል ታሪክ ምን ያስተምረናል? የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እንበላለን?
9. ዛሬ በተማርከው ታሪክ መሠረት አንድ ዳግመኛ የተወለደ ክርስቲያን ማድረግ የሚፈልገው ነገር ምንድነው?
10. ዛሬ እግዚአብሔር አንተን የሚያስተምርህ ምንድነው? ከዚህ ታሪክ የተነሣ በዚህ ሣምንት ምን ታደርጋለህ?

**የቃል ጥናት ክፍል፡- 1ጴጥ፡2፡2፡-**
ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ፡፡

## ትምህርት-3

**በእግዚአብሔር ቃል ማደግ**

***መግቢያ፡-*** በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚረዳን ባለፈው ሣምንት ተምረን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሰዎች በየጊዜው የእግዚአብሔርን ቃል ላለማንበባቸው የተለያዩ ምክንያቶችን ይሰጣሉ፡፡ ዛሬ የእግዘአብሔርን ቃል እንድናነብ የሚያበረታቱንን ጥቅሶች እንመለከታለን፡፡

1. ምሳ፡2፡1-5 አንብብ፡፡ በዚህ ክፍል የእግዚአብሔር ቃል በምንድነው የተመሰለው? ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት በማድረግ እንድታድግ የሚረዳህ ምንድው?
2. አንተ በግል ሕይወትህ የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ እንዴት ጥረት እንደምታደርግ ግለጽ፡፡
3. በቤተሰብ፣በገንዘብ፣ለሌሎች ጥንቃቄ በመውሰድ እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች ላይ ያለህን አስተሳሰብ የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ቀየረ?
4. ጊዜ ወስደህ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳታነብ ተግዳሮት የሆኑትን ነገሮች ለውይይት አቅርብ፡፡
5. እነዚህን ተግዳሮቶችን እንዴት ማሸነፍ እንችላለን?
6. ዘዳ፡17፡19 አንብብ፡፡ ከዚህ ክፍል ትማራለህ?

ቃሉን ለማንበብ የሚረዱ ሀሳቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ ለውይይት አቅርባቸው፡፡

1. በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የጊዜ ፕሮግራም አውጣ፡፡
2. ፀጥታ ያለውን ቦታ ምረጥ፡፡
3. የምታነበውን እንድትረዳ እግዚአብሔር ልብህን እንዲከፍት ፀልይ፡፡
4. ያነበብከውን ከሕይወትህ ጋር ማዛመድ እንድትችል እግዚአብሔር እንዲረዳህ ፀልይ፡፡
5. ያነበብከውን እውነት ለሌሎች ለማካፈል ፈቃደኛና ዝግጁ ሁን፡፡

**<u>የቃል ጥናት ክፍል፡-</u> 1ጴጥ፡2፡2፡-**

ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ፡፡

## ትምህርት-4

**የአባት ተግሣጽ**

***ለመሪው፡-*** የዛሬው ታሪክ የመጽሐፉን ጭብጥ ሀሳብ በመያዝ እንደ አንድ አዲስ ታሪክ እንዴት መናገር እንደምትችል ያሳያል፡፡ መሪ እንደመሆንህ መጠን ከላይ በመግቢያ ላይ የተገለጹትን መመሪያዎች በመጠቀም ታሪኩን መናገር ያስፈልግሃል፡፡

**ይህን ታሪክ ከተማርክ በኋላ በቃል ተናገር፡-** ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ ደቀመዛሙርቱ የምስራቹን ወንጌል ለብዙ ሕዝብ ሰበኩ፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አይሁድ በኢየሱስ አምነው እርሱን መከተል ጀመሩ፡፡ ካመኑት አይሁድ የተወሰኑቱ ተሰደዱ፡፡

ሌሎቹ ሞቱ፡፡ ከዚህ የተነሣ በኢየሱስ ማመናቸው ጥያቄ ስለፈጠረባቸው እግዚአብሔር መልእክተኛን ላከ፡፡ የዚህን መልእክተኛ ስም አናውቅም፡፡ ነገር ግን መጽሐፉ የዕብራዊያን መልእክት ይባላል፡፡ ይህ የዕብራዊያን መልእክት እነርሱን የእግዚአብሔር ልጆች ይላቸዋል፡፡ እንዲህም ሲል፡-

‹‹ልጄ ሆይ የጌታን ቅጣት አታቅልል በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ጌታ የሚወደውን ይቀጣልና የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፋዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል፡፡ ለመቀጣት ታገሡ፤ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም፡፡ ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸውም ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን? እነርሱ መልካም ሆኖ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል፡፡ ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል፡፡››

እነዚህና ሌሎች የዕብራዊያን መልእክቶች እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነታቸውን እንዲያጠብቁና እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው እንዲያውቁ ያበረታቱአቸው ነበር፡፡

**ዕብ፡12፡1-11 አንብብ፡፡**

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ልጆቹን የማይገሥጸው ምን ዓይነት አባት ነው?
2. ልጆቹን የሚወድ አባት ልጆቹን የሚገሥጸው መቼ ነው?
3. በልጅነትህ አባትህ ሲገሥጽህ ሁሌ ደስ ይልህ ነበር? የአባትህ ተግሣጽ ጠቅሞሃል?
4. የእግዚአብሔር ተግሣጽ ከምድራዊ አባቶች ተግሣጽ በምን ይለያል?
5. ለእግዚአብሔር ተግሣጽ የመጨረሻው ግብ ምንድነው?
6. በሕይወታችን ችግር ሲገጥመን አመለካከታችን ምን መሆን አለበት?
7. የዚህ ታሪክ እውነት ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት እንድታድግ እንዴት ይረዳሃል?
8. ዛሬ እግዚአብሔር ምን ያስተምርሃል?

**የቃል ጥናት ክፍል፡ ቆላ፡3፡16፡-**

የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡፡

## ትምህርት-5

**ፀሎት፡- ዳንኤል**

**መግቢያውን አንብብ**፡- ዳንኤል እሥራኤላዊ ሲሆን በምርኮ ወደ ባቢሎን የተወሰደ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ በመጨረሻ በባቢሎን መንግሥት ውስጥ መሪ ሆነ። ይህ እየሆነ ባለበት ሰዓት ንጉሡ ዳሪዮስ እሱን በመንግሥቱ ሁሉ ላይ ሊሾመው አቀደ። ሌሎች መሪዎች ይህንን አይተው በዳንኤል ላይ ቀኑ። ከእሱ ምንም ጥፋት ሊያገኙ አልቻሉም። ይልቁን ለአምላኩ ታማኝ እንደሆነ አወቁ። ስለዚህ ዳንኤልን ሊያጠፉ የሚችለውን ሕግ አወጡ። የፓሪስ ሕግ አንዴ ከፀደቀ አይሻርም። ስለዚህ መሪዎቹ ፡- ‹‹ለንጉሡና ላቆመው ምስል የማይሰግድ ሁሉ በአንበሳ ጉድጓድ ይጣላል›› የሚል ሕግ ንጉሡ እንዲያወጣ አሳመኑት። ቀጥሎ የሆነው ነገር ከዚህ በታች ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር፡- ዳን፡6፡10-24

ማን? ምን? መቼ? የት? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ስለ ዳንኤል ፀሎት ሁኔታ ምን እንማራለን?
2. የንጉሡ ትዕዛዝ በዳንኤል ፀሎት ላይ ተጽዕኖ አምጥቶ ነበር?
3. ንጉሡ ስለ ዳንኤል የሚያስበው ምን ነበር? ንጉሡ ዳንኤልን ለመርዳት ምን ማድረግ ይችል ነበር?
4. እግዚአብሔር ዳንኤልን ማዳን እንደሚችል በታሪኩ ውስጥ ካሉ ሰዎች የሚያምን ነበር?
5. ለአንተ ስላለህ የፀሎት ሁኔታ ይህ ታሪክ ምን ያስተምርሃል?
6. ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ?
7. ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትህን አጥብቀህ በመንፈሳዊ ሕይወት እንድታድግ ፀሎት እንዴት ይረዳሃል?
8. ዳግመኛ የተወለደ ሰው ማድረግ የሚፈልገው ነገር ምንድነው? ለምን?
9. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

**የቃል ጥናት ክፍል፡ ቆላ፡3፡16፡-**

የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።

## ትምህርት-6

**ኢየሱስ ስለ ፀሎት አስተማረ**

**መግቢያውን አንብብ፡-** ዛሬ ኢየሱስ ስለ ፀሎት ያስተማረውን እንማራለን። ይህን ታሪክ ከዚህ በፊት ሰምተህ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ዛሬ በአዲስ ጆሮ ስማ።

ታሪኩን ተናገር፡- ማቴ፡6፡5-13

በመጀመሪያ ምን ሆነ? ቀጥሎ ምን ሆነ? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡

ታሪኩን አንብብ፡- ማቴ፡6፡5-13

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ግብዝ የሚባለው ምን ዓይነት ሰው ነው? ግብዞች እንዴት ነው የሚፀልዩት?
2. እኛ እንዴት እንድንፀልይ ነው እግዚአብሔር የሚፈልገው?
3. ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ?
4. አህዛብ እንዴት ይፀልያሉ? ኢየሱስ እንደ አህዛብ በከንቱ አትድከሙ ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. እግዚአብሔር አባታችን ነው፤ እኛም ልጆቹ ነን፡፡ ልባችንን በፍጹም ለእግዚአብሔር እንድናሳይ ኢየሱስ ያስተምረናል፡፡ ሁል ጊዜ አንድ ዓይነት ፀሎት ሸምድደን እንድንፀልይ ኢየሱስ አይፈልግም፡፡ ልክ እንደልጆች ወደ እርሱ እንድንቀርብ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ እንዴት መፀልይ እንዳለብን ኢየሱስ መመሪያ አስቀምጦልናል፡፡ ከቁ.9-13 ድረስ ባለው ቦታ በእያንዳንዱ ቁጥር ላይ ለምን መፀለይ እንዳለብን ይጠቅሳል፡፡
    - በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ የሚለው…………. አምልኮን ያሳያል፡፡
    - መንግሥትህ ትምጣ የሚለው…………........ ለሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት መፀለይን ያሳያል፡፡
    - ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን ማለት………… ጌታና ንጉሥ ለሆነው አምላክ መገዛት ማለት ነው፡፡
    - የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን ማለት………………….የሚያስፈልገንን ስጠን ማለት ነው፡፡
    - በደላችንን ይቅር በለን የሚለው…………………….. ንስሐ መግባትን ያሳያል፡፡
    - ወደ ፈተና አታግባን ማለት…………………… ሐጢአት እንዳናደርግ ጠብቀን ማለት ነው፡፡
    - ከክፉ አድነን ማለት…………………………… ከዚህ ዓለም ክፋት ሰውረን ማለት ነው፡፡
6. ይህ የፀሎት መመሪያ ለፀሎታችን እንዴት እንደሚረዳን ተወያዩ፡፡
7. ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት ማወቅ በፀሎትህ እንዴት ሊረዳህ ይችላል?
8. ዛሬ የተማርከው ምንድነው? የፀሎትህን መንገድ እንዴት መቀየር ትችላለህ?
9. ስለ ፀሎት ያለህ ጥያቄ ምንድነው?

**የቃል ጥናት ክፍል፡ ቆላ፡3፡16፡-**

የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡፡

## <u>ትምህርት-7</u>

## <u>ሕብረት</u>

**<u>መግቢያውን አንብብ</u>፡-** *መንፈስ ቅዱስ በሐዋሪያት ላይ ከመጣ በኋላ ሐዋሪያው ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ለብዙ ሕዝብ ወንጌልን ሰበከ። ሕዝቡ በስብከቱ ተነቃቅተው ‹‹ምን እናድርግ?›› ብለው ጠየቁት። ወዲያውም ቤተክርስቲያን ተወለደች። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።*

**ታሪኩን ተናገር፡-** ሐዋ፡2፡37-47

*ማን? የት? መቼ? ምን? ምን ያህል? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።*

**ታሪኩን አንብብ።**

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ለመጨመር ያደረጉት ምን ነበር? አንተስ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ለመጨመር ምን ማድረግ አለብህ?
2. ንስሐ መግባት ማለት ምን ማለት ነው?
3. በጴጥሮስ ስብከት ወደ 3000 የሚያህሉ ሰዎች ጌታን ተቀበሉ። እነዚህ ጌታን የተቀበሉ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን የተጨመሩት መቼ ነበር?
4. የአዲሲቷ ቤተክርስቲያን ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበረ ግለጽ። አዲስ ጌታን የተቀበለ ሰው ለማድረግ የሚፈልገው ምን ነበር?
5. አዲስ ክርስቲያኖች ስለ አዲስ ሕይወት የሚማሩት እንዴት ነበር? እነዚህ ክርስቲያኖች በአንድ ነገር ላይ መወሰንን፣እርስ በርስ ግንኙነት ማድረግንና ወደ ቡድኑ መጨመርን እንዴት ነው የተማሩት?
6. የሐዋሪያት ትምህርት እንዴት አዲሶቹን ክርስቲያኖች ረዳቸው? ሐዋሪያት በዚያን ጊዜ የማንን ታሪክ ይናገራሉ ብለህ ታስባለህ?
7. ቤተክርስቲያን ልክ አዲስ አማኞች የሚጨመሩበት እንደ ቤተሰብ ያለ ቦታ ነው። የአንድ ቤተሰብ አባላትን አስብ። አንድ ሕፃን በቤተሰብ ቁጥር የሚጨመረው መቼ ነው? አንድ ጤናማ አስተዳደግ ለሚያስፈልገው ሕፃን የወላጆች ፍቅር ምን ያህል አስፈላጊ ነው? አንድ ሕፃን የወላጆቹን ፍቅር ሳያገኝ ቢያድግ ምን ይሆናል? ለአንድ ሕፃን የሚያስፈልገው ነገር እንዴት ነው የሚሟላው? ለአንድ አዲስ ክርስቲያን የሚያስፈልገው ነገር በቤተክርስቲያን እንዴት ነው ሲሟላ የነበረው?
8. አንተ የዚያች ቤተክርስቲያን አባል ብትሆን ኖሮ ምን ይሰማህ ነበር?
9. በዕብ፡10፡24-25 ላይ ያለውን የቃል ጥናት ክፍል ከዚህ ታሪክ ጋር በማስተያየት ተወያይ።
10. ከዚህ ታሪክ የተማርከውን እውነት በዚህ ሣምንት እንዴት ከሕይወትህ ጋር ታዛምዳለህ?

**የቃል ጥናት ክፍል፡ ቆላ፡3፡16፡-**

የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡፡

## <u>ትምህርት-8</u>

### <u>ስለ መስጠት</u>

**<u>መግቢያውን አንብብ፡-</u>** ስለ ቤተክርስቲያን ፈጣን እድገት ባለፈው ሳምንት ተምረን ነበር፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አማኞች እርስ በርስ በመዋደዳቸው በማህበረሰቡ ውስጥ ብርሃን ሆነው ነበር፡፡ ተጨማሪው ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡- ሐዋ፡4፡32-37

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡

ታሪኩን አንብብ፡፡

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. በቁ.32 ላይ ያለችው ቤተክርስቲያን ምን እንደምትመስል ግለጽ፡፡
2. አማኞች በአንድ ልብ መሆናቸውን እንዴት ገለጹ?
3. ስለ ባርናባስ ምን እንማራለን?
4. በዚህ ታሪክ መሠረት አማኞች እንዴት መኖር ይፈልጉ እንደነበር ግለጽ፡፡
5. በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ ችግረኛ ሰው አልነበረም፡፡ ሕዝቡ ከእኔነት መንፈስ ወጥተው ለሌሎች እንዲያስቡ እግዚአብሔር የሕዝቡን አመለካከት እንዴት እንደቀየረ ተወያዩ፡፡
6. መስጠት ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ማደግ እንድንችል እንዴት ይረዳናል?
7. 2ቆሮ፡9፡7 አንብብ፡- ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ? ስለ መስጠት ምን ትማራለህ?
8. ስለ ግል ቁሳዊ ንብረትህ ምን ይሰማሃል?
9. ለመስጠት ከራሳችን ጋር ልንታገል እንችላለን፡፡ ሰዎች በየጊዜው አሥራትንና ሌሎች ስጦታዎችን በታማኝነት ስለ ሰጡ በሕይወታቸው ስለ ተለማመዷቸው በረከቶች ተወያዩ፡፡
10. ዛሬ እግዚአብሔር ምን እያስተማረህ ነው?

**የቃል ጥናት ክፍል፡ ቆላ፡3፡16፡-**

የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡፡

## ትምህርት-9

**አዲስ ትዕዛዝ**

**መግቢያውን አንብብ**፡- በዛሬው ታሪክ ኢየሱስ በቅርቡ በመስቀል ላይ እንደሚሞት ያውቅ ነበር፡፡ ስለዚህ ደቀመዛሙርትን ለመጨረሻ እራት ጊዜ ሰብስቦ ያስተምራቸው ነበር፡፡ የኢየሱስ የመጨረሻ ንግግር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ፍቅር በጣም አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ደቀመዛሙርቱ እንዲረዱ ፈለገ፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡- ዮሐ፡1-17 እና ቁ.34-35

ማን? መቼ? የት? ምን? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ተናገር::

ታሪኩን አንብብ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ኢየሱስ ፍቅሩን ለደቀመዛሙርቱ እንዴት አሳየ?
2. ይህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምራል?
3. አዲሱ ትዕዛዝ ኢየሱስ እንደሚወድ ሌሎችን መውደድ የሚል ነበር፡፡ ይህ መውደድ ምን ዓይነት እንደሆነ ግለጽ፡፡
4. ወንድሞች እርስ በርስ ቢዋደዱ ውጤቱ ምን ይሆናል? ቁ.35
5. እርስ በርስ መዋደዳችን ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት እንድናድግ እንዴት ይረዳናል?
6. ጥላቻ፣መከፋፈልና ቅንዓት ዛሬም በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳለ ሰዎች ያያሉ ወይስ ለሌሎች በምታሳዩት መውደድ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እንደሆናችሁ ነው የሚያውቁት? ስለዚህ ጉዳይ ተወያዩ፡፡
7. ይህንን ታሪክ በዚህ ሳምንት እንዴት ከሕይወትህ ጋር ታዛምዳለህ?

**ዕብራ፡10፡24-25፡-**

ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ፡፡

## ትምህርት-10

**ወንድሞችን መውደድ**

**መግቢያውን አንብብ፡-** ኢየሱስ ስለ ፍቅር ብዙ ጊዜ አስተምሯል፡፡ ‹‹ብትወዱኝ ትዕዛዜን ትጠብቃላችሁ፤ሌሎችንም ትወዳላችሁ›› ብሏል፡፡ በየቀኑ ሌሎችን በቀላሉ ለመውደድ ማድረግ የምንችለውን ነገር ለማስተማር ኢየሱስ ምሳሌ ተጠቅሟል፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡- ማቴ፡25፡31-46

**የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ተናገር**

1. የሰው ልጅ የፍርድ ወንበር ምን እንደሚመስል ግለጽ፡፡
2. ኢየሱስ ሰዎችን ወደፊት እንዴት ነው የሚለያቸው?
3. ንጉሡ በቀኙ ላሉ ሰዎች ምን ይላቸዋል?
4. በቀኙ ያሉ ሰዎች ለእሱ ምን አደረጉለት?

5. ፃድቃንም መልሰው ምን አሉት?
6. ንጉሡ በግራው በኩል ለቆሙት ምን ይላቸዋል?
7. በግራው የቆሙት ያላደረጉት ምንድነው?
8. እነርሱ መልሰው ምን አሉት?
9. ለእነዚህ ሁለት ቡድን ሰዎች በመጨረሻ የሚሆነው ምንድነው?

ታሪኩን አንብብ፡፡

<u>**የውይይት ጥያቄዎች**</u>

1. የእምነታችን እውነተኛው ማረጋገጫ ምንድነው?
2. ሌሎችን ለመርዳት ማድረግ የምንችላቸው ነገሮች ምንድናቸው?
3. እነዚህ የርህራሄ ተግባራት ሀብትን፣ችሎታንና ዕውቀትን መሠረት ያደረጉ ነበሩ፡፡ በዚህ ታሪክ መሠረት ሌሎችን ላለመርዳታችን ልንሰጥ የምንችለው ማስተባበያ አለ?
4. ይህ ታሪክ ትኩረት የሚያደርገው ምን ላይ ነው?
5. ይህንን ታሪክ በዚህ ሳምንት በሕይወትህ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ ትችላለህ?

<u>የቃል ጥናት፡-</u> **ዕብራ፡10፡24-25፡-**
ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ፡፡

## <u>ትምህርት-11</u>

<u>**አገልግሎት፡ ሐዋ፡9፡32-43**</u>

<u>**መግቢያ**</u>፡- የዛሬው ታሪካችን ስለ ዶርቃ ነው፡፡ በቤተክርስቲያን መጀመሪያ የኖረች ሴት ነች፡፡ ይህ አበረታች ታሪክ ከሐዋሪያት ሥራ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ ሐዋ፡9፡32-43
የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡

1. ዶርቃ ያደረገችው ነገር ምንድነው
2. በእርሷ ላይ የሆነው ነገር ምንድነው
3. በእርሷ ከተማ አቅራቢያ ይኖር የነበረው ማነው
4. የቤተክርስቲያን ሰዎች ምን አደረጉ
5. ቀጥሎ ምን ሆነ
6. መበለቶች ለጴጥሮ ያሳዩት ነገር ምንድነው (መልሱ፡- የሞተችው ዶርቃ ለእነርሱ የሠራችሁን ልብሶችን አሳዮት፡፡)
7. ጴጥሮስ ምን አደረገ
8. የዚህ ተአምር ውጤቱ ምን ነበር

ታሪኩን አንብብ፡፡ የተረሳ ነገር አለ

<u>**የውይይት ጥያቄዎች**</u>

1. ዶርቃ ሌሎችን ለማገልገል በተግባር ያደረገችውን አገልግሎት ተወያዩ፡፡ ቁ.39
2. በአቅራቢዋ የነበሩ ሰዎች ስለ እርሷ ምን ይሰማቸው ነበር?
3. እግዚአብሔር ዶርቃን ከሞተችበት ያስነሣው ለምን ይመስልሃል? ይህ ስለ እርሷ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ምን ያስትምረናል? እግዚአብሔር ለድሆች ስላለሁ ሰፊ ልብ ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?
4. ከሥራህ ጋር ታግለህ ታውቃለህ? አንዳንድ ጊዜ ከዚህ የበለጠ ሥራ በኖረኝ ብለህ ታውቃለህ? ይህ ታሪክ እንዴት ሊያበረታታህ ይችላል?
5. ሌሎችን ማገልገል ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት እንድታድግ እንዴት ይረዳሃል?
6. ከዚህ ታሪክ የተነሣ ሕይወቴ እንዴት መቀየር አለበት ትላለህ?

<u>የቃል ጥናት፦</u> **ዕብራ፡10፡24-25፦**
ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ፡፡

## <u>ትምህርት-12</u>

### <u>የአባትን ፈቃድ ማድረግ</u>

**<u>መግቢያ</u>**፦ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ጌሊላ ሄደ፡፡ ከዚያም ስለ ደከመው በሰማሪያ አንድ ውሃ ያለበት ጉድጓድ ዳር እንደደረሰ ተቀመጠ፡፡ ደቀመዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው ነበር፡፡ አንዲት ሴት ውሃ ልትቀዳ መጣች፡፡ ኢየሱስ በዚያ ክርስቶስ እንደሆነ ስለራሱ ነገራት፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ ዮሐ፡4፡27-38
ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡

### <u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ እንዲበላ ለመኑት፡፡ ኢየሱስ ምን አላቸው? የእርሱ ምግብ ምን ነበር?
2. መንፈሳዊ ምግብ መጽሐፍ ቅዱስን፣ፀሎትንና አምልኮን ያካትታል፡፡ መንፈሳዊ ምግብ በመብላት ስለምናገኘው እድገት ይህ ታሪክ ምን ያስተምረናል?
3. በዚህ ታሪክ የኢየሱስ ሥራ ምንድነው?
4. እኛ ሁላችንም የምንፈልገውና የምንመኘው ነገር አለ፡፡ ይህንን እግዚአብሔር ያውቃል፤ደግሞም ይረዳዋል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን እንደዚህ ነው የፈጠረን፡፡ ነገር ግን ፍላጎታችንን ለዘላለም ሊያረካ የሚችል እርሱ ብቻ እንደሆነ እኛ እንድናውቅ ይፈልጋል፡፡ እርካታን የበለጠ ሊሰጥ የሚችለው ምንድነው? ይህ የምንጠጣው ውሃ ነው ወይስ የሕይወት ውሃ ነው? ይህ የምንበላው እንጀራ ነው ወይስ የሕይወት እንጀራ ነው? በልብህ ጥልቅ ምኞት የተመኘህበትን ጊዜ ተናገር፡፡
5. ዮሐ፡17፡1-4፡፡ ይህ የሆነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት ነው ኢየሱስ የፈጸመው ሥራ ምንድነው?

6. የኢየሱስን ምሳሌ እንዴት መከተል እንችላለን?
7. አንድ አዲስ አማኝ ሊያደርገው ስለሚመኘው ነገር ከዚህች ሴት ሕይወት ምን እንማራለን?
8. ዛሬ እግዚአብሔር  አንተን የሚያስተምርህ ምንድነው?

<u>አስተያየት፦</u> ከእግዚአብሔር ጋር በቀረበ ግንኙነት መኖር እርካታ ነው፡፡ ይህ የሚያካትተው እግዚአብሔር የሚሠራውን ማየትና አባት የሚሠራውን አይቶ መሥራትን ነው፡፡ ይህም የሚጠፉ ነፍሳትን ወደ ቤቱ ማምጣት ነው፡፡ ኢየሱስ የአብን ፈቃድ ለዘላለም በማገልገሉ ታላቅ እርካታን አገኘ፡፡

<u>የቃል ጥናት፡</u> ገላ፡6፡10፦እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ፡፡

## <u>ትምህርት-13</u>

## <u>የኤልሳዕ ከአለቃው (ጌታው) ጋር መቆየት</u>

<u>መግቢያ</u>፦ ኤልያስ ታላላቅ ተአምራትን የሠራ ሃይለኛ ነቢይ ነበር፡፡ ኤልሳዕ የኤልያስ አገልጋይ ነበር፡፡ ለኤልያስ የነበረውን የነቢያት መሪነት አገልግሎት ኤልሳዕ ለማስቀጠል ፈለገ፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ፈለገ፡፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ 2ነገ፡2፡1-15
የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የታሪኩን እውኔታ ግልጽ ለማድረግ ሞክር፡፡
አሁን ታሪኩን አንብብ፡፡

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ስንት ጊዜና ቦታ ነው ኤልያስ ኤልሳዕ ከእርሱ ጋር እንዳይሄድና ባለበት እንዲቆይ የነገረው? ኤልሳዕ ለዚህ ሁሉ የሰጠው ምላሽ ምንድነው?
2. ኤልሳዕ ማቆም ይችል ነበር፤ እግዚአብሔር በእነዚያ ቦታዎች ሊጠቀመቀው ይችል ነበር፡፡ ከሌሎች ነቢያት ጋር ሆኖ ማረፍ ይችል ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ለምንድነው ለመሄድ የቆረጠው?
3. ኤልሳዕ ከጌታው ጋር በመቆየቱ ያየው ነገር ወይም የተለማመደው ነገር ምንድነው?
4. ኤልያስ ንጹሕ አመለካከት ነበረው፡፡ እርሱ ኤልሳዕን ሲጠይቀው የነበረው ሁሉ ለራሱ ክብርን ለማግኘት ሳይሆን የበለጠውን የእግዚአብሔር ሥራ ይሠራ ዘንድ በመፈለጉ ነው፡፡ ታላላቅ ሥራዎችን ለመሥራት እግዚአብሔርን እንዳትጠይቅ የሚከለክልህ ነገር ምንድነው?
5. እኛ በዚህ ታሪክ ውስጥ ራሳችንን ማየት እንችላለን፡፡ በሚመቸን ሥፍራ ኢየሱስን ተከትለናል፡፡ አሁን ከፊታችን ምርጫ አለ፡፡ ልክ በኢያርኮና በቤቴል እንደነበሩ ነቢያት ተመቻችተን መቀመጥ ወይም እንደ ኤልሳዕ መንገዱን አልፎ ለመሄድ መቁረጥ፡፡ ቀኖችህን በሙሉ ባለበት ቦታ የሚያስከድ ክርስትና ነው የምትፈልገው ወይስ ከዚህ የበለጠውን ሕይወት መለማመድ?
6. ይህንን ታሪክ ከሕይወትህ ጋር እንዴት ማዛመድ ትችላለህ? በመንፈሳዊ ሕይወት እንድታድግ የሚረዳህ ምንድነው?

7. እግዚአብሔር በአንተ ሕይወት በሃይል ሊሠራ ከአንተ የሚፈልገው ነገር ምንድነው?

__*የቃል ጥናት:*__ *ገላ*:6:10፡-እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።

## __ትምህርት-14__

__*ዮናታንና ዳዊት*__

__*መግቢያ*__፡- የዮናታንና ዳዊት ታሪክ አስደናቂ ነው። ነገር ግን ታሪኩን ለመረዳት የታሪኩን አውድ (context) ሰፋ አድርገን መመልከት ያስፈልገናል። ዮናታን ወደ ዳዊት ከመምጣቱ በፊት ምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልገናል። ዮናታን የንጉሡ ሳዖል ልጅ ነው። ጠላቶችን ተዋግቶ በማሸነፉ ምክንያት የሕዝቡን ልብ የማረከ የጦር ጀግና ነበር። ከአባቱ በኋላ ቀጣይ ንጉሥ ለመሆን ተዘጋጅቶ ነበር። በዚህ ጊዜ የዳዊት ታሪክ በመሃል ገባ። ዳዊት ጎሊያድን ተዋግቶ አሸነፈ። አሁን ዳዊት ጀግና ነው። በዚህ ጊዜ ዮናታን ወደ ዳዊት መጣ። አንዱ ለሌላው ካሳዩት ፍቅር ብዙ የምንማረው ነገር አለ። ታሪኩ ቀጥሎ ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር። 1ሳሙ፡18፡1-4

በመጀመሪያ ምን ሆነ? ቀጥሎ የሆነው ምንድነው? እንዲሁም ማን? ምን? ወዘተ የመሳሰሉትን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ከልስ።
ታሪኩን አንብብ።

__*የውይይት ጥያቄዎች*__

1. ዮናታን እንዴት ነው ዳዊትን ቶሎ ወዳጁ ያደረገው?
2. እነዚህን ሰዎች በፍጥነት ለመወዳጀት ያበቃው ምንድነው? ሁለቱን አንድ የሚያደርጋቸው ምንድነው? ስለ ውጊያቸውና ለእግዚአብሔርና ለእሥራኤል ሕዝብ የነበራቸውን ፍቅር አስብ።
3. ዮናታን ለዳዊት የሰጠው ምንድነው? ይህ ምንን ይወክላል?
4. ዮናታን የንጉሥ ልጅ እንደመሆኑ መጠን ዳዊትን ያገለግል ነበር? ከዚህ ምሳሌ የምትማረው ምንድነው?
5. 1ሳሙ፡23፡15-18 አንብብ። ዮናታን የሚያውቀው ምንድነው? እግዚአብሔር ዳዊትን በመምረጡ የዮናታን ምኞትና ሕይወት እንዴት ተቀየረ?
6. በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊኖር ስለሚገባው የእርስ በርስ ወዳጅነት ይህ ታሪክ ምን ያስተምርሃል?

__*የቃል ጥናት:*__ *ገላ*:6:10፡-እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።

## ትምህርት-15

**እርስ በርስ መዋደድ**

*መግቢያ፡- ዳዊት በእግዚአብሔር የተመረጠ ንጉሥ እንደሆነ ዮናታን ያውቃል። ይህንን ተቀብሎ ዳዊትን ይወደው ነበር። በቤተክርስቲያን ውስጥ በመካከላችን ያለው ግንኙነት የተመሠረተው በእግዚአብሔር ምርጫ ነው። የዛሬው ታሪክ ትኩረት የሚያደርገው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ቢሆንም ለወንድሞች በምናሳየው መውደድ ላይ ነው። ከዮናታን ሕይወት ብዙ መማር እንችላለን። አባቱ ሳዖል በዳዊት ላይ ቀንቶ ሊገድለው ፈለገ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እደሚከተለው ቀርቧል።*

*ከአባላቱ አንድ ሰው የታሪኩን የመጀመሪያውን አጋማሽ እንዲናገር አድርግ።* 1ሳሙ፡19፡1-7
*ሌላ ሰው ደግሞ ሁለተኛውን አጋማሽ እንዲናገር አድርግ።* 1ሳሙ፡20፡1-42
*የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ከልስ።*
*ሁለቱንም ታሪኮች አንብብ።*

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. *ሳዖል ዮናታን እንዲያደርግለት አጥብቆ የሚፈልገው ምንድው?*
2. *ዮናታን ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሰው መሆኑን ለማሳየት ያደረገው ምንድነው?*
3. *መከራና ስደት ሲመጣ ዮናታን ምን ያህል ርቀት መሄድ አለበት?*
4. *ዮናታንን የገጠሙት ጉዳዮች ምንድናቸው? በክርስቶስ የሚያምን አዲስ አማኝን ሊገጥሙት የሚችሉ ተመሳሳይ ጉዳዮች ምንድናቸው?*
5. *ዮናታን ዳዊትን እንዴት ነው ያጽናናው?*
6. *ይህንን ግንኙነት እንደ ምሳሌ በመውሰድ ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ምን መሆን እንዳለበት ተወያዩ።*
7. *እግዚአብሔር ዳዊትን ቀጣይ ንጉሥ አድርጎ መረጠው። ዛሬም ሰዎችን መርጦ በቤክርስቲያን ውስጥ ያስቀመጠው እግዚአብሔር ነው። የዮናታንን ምሳሌ በመከተል በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን አባላት እንዴት መርዳት ትችላለህ? የምታገኛቸውን አጋጣሚዎች አንድ በአንድ ለመጠቀም ሞክር።*
8. *እግዚአብሔር ዛሬ የሚያስተምርህ ምንድነው?*

***መዝ*:92፡1-2፡-*እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው ልዑል ሆይ ለስምህም ዝማሬ ማቅረብ በማለዳ ምሕረትን በሌሊትም እውነትህን ማውራት።***

## ትምህርት-16

**አምልኮ**

***መግቢያ***፡- *አይሁድ እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ብዙ የአምልኮ መመሪያዎችን ሰጣቸው። ነገር ግን ጊዜ እየጨመረ ሲሄድ የሕዝቡ ልብ ከእግዚአብሔር በመራቁ አምልኮው በየጊዜው የሚደረግ የመንጻት ሥራ ሆነ። ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ አምልኮ በመንፈስና በእውነት መሆን እንዳለበት አስተማረ። ዛሬ ስለ አምልኮ የበለጠውን እንማራለን።*
*ሮሜ*፡12፡1 *አንብብ። እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኊለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።*

1. *ለእግዚአብሔር የምንሰዋው ምንድነው? ከዚህ ጥቅስ ስለ አምልኮ የምንማረው ምንድነው?*

2. አምልኮ ከዝማሬና ከስሜታዊነት ያልፋልን?
3. አምልኮ በብዙ መንገድ ይገለጻል። ምስጋናና ውዳሴን ለእግዚአብሔር ከማቅረብ ጋር ይያያዛል። ሁለቱንም እጆች ወደ ላይ ዘርግቶ በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኮ የሚፀልይ አንድ ሰው አስብ፤ አንድ እጁ ምስጋናን ለእግዚአብሔር ሲያቀርብ ሌላው እጁ ውዳሴን ያቀርባል። ውዳሴ በእግዚአብሔር ማንነት ላይ ትኩረት ሲያደርግ ምስጋና ደግሞ እግዚአብሔር ባደረገው ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ ነው።
4. ዕብ፡13፡15 እና ኤፌ፡5፡18-20 አንብብ። እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለብን ከእነዚህ ክፍሎች የምንማረው ምንድነው?
5. ሐዋ፡16፡25 አንብብ። ጳውሎስና ስላስ በእሥር ቤት በሰንሰለት ታሥረው ይደበደቡ ነበር። እነርሱ ያደረጉት ምን ነበር? እነርሱ ትኩረት ያደረጉት በማን ላይ ነበር? ይህ ትኩረታቸው በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸውን እምነት እንዴት ጨመረላቸው?
6. መቼ ማምለክ እንዳለብን ከዚህ ምን እንማራለን?
7. እግዚአብሔር ዛሬ የሚያስተምርህ ምንድነው?

**መዝ፡92፡1-2፦**እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው ልዑል ሆይ ለስምህም ዝማሬ ማቅረብ በማለዳ ምሕረትን በሌሊትም እውነትህን ማውራት።

## ትምህርት-17

### አምልኮ

**መግቢያ**፦ አምልኮ ማለት እግዚአብሔርን አምላካችንና ጌታችን አድርገን በላያችን መሾምና ያለ እርሱ ሌላ አለማየት ማለት ነው። በሁሉም ጊዜ እግዚአብሔርን በእውነት ለማምለክ እርሱን ማወቅ ያስፈልገናል። ስለ እውነተኛው አምልኮ ዛሬ የበለጠውን እንማራለን።

1. መዝ፡100 አንብብ።
2. የቡድኑ አባላት በዚህ ክፍል ላይ ያሉትን ድርጊትን የሚያመለክቱ ቃላቶችን (ግሦች ወይም verbs) በሌላ ወረቀት ላይ እንዲዘረዝሩ አድርግ።
   ሀ. ቁ.1____________________________________________

   ለ. ቁ.2_________________________እና____________________

   ሐ. ቁ.3_______________________________

   መ. ቁ.4 ላይ አራት ነገሮች__________________________________________
3. ከዚህ መዝሙር ስለ አምልኮ የምትማረው ምንድነው?
4. መዝ፡22፡3 አንብብ። እኛ በምናመልክበት ጊዜ እግዚአብሔር የት ይሆናል?
5. መዝ፡27፡4 አንብብ። ዳዊት ከምንም ነገር አብልጦ የሚመኘው ምንድው? ስለ አምልኮ ምን ትማራለህ?
6. እግዚአብሔር ዛሬ የሚያስተምርህ ምንድነው?

**የቃል ጥናት ክፍል፦መዝ፡92፡1-2፦**እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው ልዑል ሆይ ለስምህም ዝማሬ ማቅረብ በማለዳ ምሕረትን በሌሊትም እውነትህን ማውራት።